ስሐ፡ገብቶ፡የሚድኑም፡አሉ፡
የቀደመውን፡ኃጢአታቸውን፡
ጠልተው፡የረከሰች፡የዝሙ
ታቸውን፡ልብስ፡የተዉ፡አሉ፤
ያዕ፡፭፡፲፱፡፳፡ራእ፡፫፡፬።

፳፬ መድኃኒታችን፡እግዚአብሔ
ርም፡ያለ፡ኃጢአት፡ይጠብቃ
ችሁ፡ዘንድ፡ንጹሐን፡ሁናችሁ
ም፡በጌትነቱ፡ፊት፡በደስታ፡ያ
ቆማችሁ፡ዘንድ፡ይቻለዋል። ፩
ተሰ፭፡፳፫፡ፊል፡፩፡፲።

፳፭ በጌታችን፡በመድኃኒታችን፡በ
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡'ሥልጣን፡
ለርሱ፡ምስጋና፡ይሁን።
ጌትነትም፡ኃይልና፡ሥልጣን፣
ም። ዓለም፡ከተፈጠረ፡ጀምሮ፡
ዛሬም፡ዘወትርም፡እስከ፡እሚ
መጣው፡ሁሉ። አሜን።

የያዕቆብ፡ወንድም፡የይሁዳ፡
መልክት፡ተፈጸመ። ሮሜ
፲፯፡፳፯፡፩፡ጢሞ፡፩፡፲፯። ።
ለእግዚአብሔር፡ምስጋና፡ይ
ግባው። ። ። ። ።

## ራእዩ፡ለዮሐንስ።

### የመጺናዩቱ፡የቍስጥንጥንያ፡ኤጲስ፡ቆጶስ፡ዮሐንስ፡አፈወርቅ ቱሰጸ፡የነበረ፡ጊዜ፡ያገኘው።

### ምዕራፍ፡፩።

የቍ ስጥንጥንያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዮሐንስ፡
አፈ፡ወርቅ፣ ፍጥሞ፡በምትባለው፡ደሴ
ት፡ተሰደ፡ሳለ፤ዮሐንስ፡ወንጌላዊ፡ያየው፡የ
የራዕይ፡መጽሐፍ፡አማኞች፡እንደ፡ጻፈው፤ራ
እዩም፡የተገለጸለት፡እሑድ፡ቀን፡እንደ፡ሆነ።

፩ ዮሐንስ፡ወንጌላዊ፡ያየው፡ራ
እይ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡እንዲ፡
አየው፡መጠን፡ፈጥኖ፡ይሆን፡ዘ
ንድ፡ያለውን፡ከዚያም፡በኋላ
የሚመጣውን፡ለባሮቹ፡ይገ
ልጥላቸው፡ዘንድ፡እግዚአብ
ሔር፡የገለጠለት፡ነው። ቍ፲፱፡ም፳
፪ ፪፡፯፡፯። በመልአኩ፡እጁ፡ወደ
ባርያው፡ወደ፡ዮሐንስ፡የላከው
ስለ፡እግዚአብሔር፡ቃልና፡ስለ
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፣ምስክር፡ያ
የው፡ሁሉ፡ላይ፡ምስክር፡የሆ
ነ፡ ቍ፱፡ም፡፳፡፱።
፫ የሚያነበው፡የትንቢቱንም
ቃል፡የሚሰማ፡በውስጡ፡የተ
ጻፈውንም፡የሚጠብቅ፡የተ
መሰገነ፡ነው፡ዘመኑ፡ቀርብ፡ነ
ውና። ም፳፪፡፯፡ም፳፪፡፲።
፬ ከዮሐንስ፡በእስያ፡ላሉ፡ለሰባቱ
አብያተ፡ክርስቲያናት፡ተጻፈ
ቀድሞ፡ከነበረው፡እንግዲህም

ኝ፡ሳክሁ፡ከደዌቱ፡ወገኘ፡የ
ምሆኝ፡ሥር፡የማበራ፡ያዋቢ
ያ፡ከክብ፡እኔ፡ነኝ፨ም፡፳፡፳፡(
ም፡፩፬፤ኢሳ፡፲፩፡፲፤ራእ፡፳፳፤ሉቃ
፩፡፸፡፹፨
፲፯ የተቀደሰ፡መንፈስ፡ያሳቸው
ም እመናኝም፡ይምጣ፡ያሉ(
ኝ፡እኔ፡ነኝ፡፡የተጠማም፡መዋ
ቶ፡የሚሻውን፡የሕይወትን፡ው
ሀ፡ያለ፡ዋጋ፡ይጠጣ፨ሮሜ፡፳፡
፳፫፡ም፡፳፬፡፪፡ኢሳ፡፶፡፳፡፪፡ዮ
፲፰ ሐ፡፪፡፲፪፨የዚህን፡መጣፍ፡
ቃል፡የሚሰማ፡ሁሉ፡በዚህ፡ሳ
ይ፡ቢጨምር፡በዚህ፡መጣፍ
የተጣፈውን፡መቅሠፍት፡

እግዚአብሔር፡እንዲጨም
ርባት፡እኔ፡ምስክር፡ነኝ፡፡ም፡
፲፱ ፲፳፡፩፡፪፡፫፨ ከዚህ ም፡መጣ
ፍ፡ቃል፡ቢያጐድል፡ከዕፀ፡ሕ
ይወትና፡በዚህ፡መጣፍ፡ከተ(
ጣፈችው፡ከተቀደሰች፡አገር
እድሉን፡እግዚአብሔር፡ያጐ
ድልባታልና፡ዘዳግ፡፬፡፪፤ና፡፪
፳ ፲፪፤ፊል፡፬፡፫፨ይህነኝም፡የ
ሰጣ፡እውነት፡ነው፡ይበላል፨በ
ውነት፡ፈጥኜ፡እመጣለሁና፡
ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ና፡ይበል፡የጌ
ታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ጸጋው፡ከናንተ፡ጋራ፡ይሁን፡
አሜን፨